# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ከነሐሴ አሥር ቀን (ማኅበረ በኵር) እስከ ነሐሴ ሃያ ስምንት ቀን
አብርሃም፣ እጓለ ቋአት፣ ደሲያት፣ ዓይነ ኲሉ ይባላል።

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ዓይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ
አንተ ትሁቦሙ ሲሳዮሙ በጊዜሁ
ትሰፍሕ የማነከ ወታጸግብ ለኲሉ እንሰሳ ዘበርዓትከ

የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል
አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ
አንተ እጅህን ትከፍታለህ
ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ

መዝ ፩፻፴፬፥፲፭-፲፮

ወንጌል፥ ዮሐ ፮፥፴፩-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይሁበነ ዝናመ በጊዜሁ
«ዝናምን በጊዜው ይሰጠናል»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፫፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፭፥፩-፲፪ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፪፥፩-፳፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# የሕይወት እንጀራ

ሰው በሕይወት ለመኖር ኃይሉን በእንቅስቃሴ ለመግለጥ መመገብ አንዱ መንገድ ነው። የሰው ልጅ የኃይል ምንጩ ምግብ ነው። ሥጋዊ ኃይሉ እንዳመጋገቡና እንደ አስተዳደጉ ይለያያል። ያለ ምግብ የሚኖር የለም። በመሆኑም በዓለም ያለው ያመጋገብ ሁኔታ ለምድራዊ ሕይወት መሰረት ነው። በአንጻሩም ሰው ሥጋና ደም ደመ ነፍስም ብቻ አይደለም፤ ሕያው ፍጥረታትም ነው እንጂ። ስለዚህ የሥጋ ቀፈቱ ቢሞላም የሕይወት እንጀራ ካላገኘ ጥሩ ሕይወት ላይኖረውም ለሚቋረጠውም ምድራዊ ሕይወቱ ምግብ ካስፈለገው ለዘላቂ ሕይወቱ የበለጠ ምግብ ያስፈልገዋል። ያ ካልሆነ ግን ጉዞው ይቋረጣል። ዓላማው አይሳካም። ሕይወቱ የተሳቀቀ ይሆናል።

**የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ነው።**

ቅዱስ ኤልያስ ኤልዛቤል አስመርራው በክትወክታዋ ስር በነበረበት ሰዓት ጌታ የተማረረች ሕይወቱን፣ ሞት የናፈቃት መንፈሱን እኔ ከአባቶቼ አልበልጥም በማለት ከመከራዋ ጽናት የተነሳ እራስዋን ዝቅ የምታደርግ እኔነቱን (እሱነቱን) ለማደስ ረጅሙ የሕይወት ጉዞ ጨርሶ ወደ እግዚአብሔር ተራራ እንዲደርስ እግዚአብሔርንም በዝምታ ውስጥ እንዲያስተውልና እንዲቀድስ እስራኤል ከተመገቡት እንጀራ የተለየ እንጀራ መገበው። ኤልያስም በረታና ከሞት አመለጠ፤ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ደረሰ። ሞትም በመንገድ አላገኘውም፤ ኤልዛቤልም ድል ተነሳች (፩ኛ ነገሥት ፲፱፥፭-፰)።

ሕዝበ እስራኤል ወደ ምድራዊት ከንዓን ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር በወደደ ጊዜ ከኤርትራ መሻገር በኋላ መናን ከላይ እየሰጣቸው ውኃን ከአለት እያፈለቀላቸው ነበር። እስራኤል ለጉዟቸው ይመገቡት የነበረው መና ክርስቲያኖች ወደ ጽዮን ለመድረስ መንፈሳዊ ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል (ዘጸ ፲፮፥፩-፴፮)።

መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በተጨማሪ ስለ ሕይወት እንጀራ በሁለት ክፍሎ ያስተምራል።

## የሕይወት እንጀራ ...

ነሐሴ ፳፫

1ኛ) የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ነው። የሕይወት እንጀራ መሆኑን እስራኤል ከበሉት መና ጋር እያነጻጸረ ሲናገር «ኢየሱስም የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል።» (ዮሐ ፮፤፵፰-፶፩) አለ። ከዚህ ላይ አንድ ነገር እንገንዘብ። ጌታ የሕይወት እንጀራ ነኝ ማለቱ ለሰው ልጆች ሕይወትነቱን ለመግለጽ ነው።

እውነት ያለ ምግብ ሊኖር የሚችል ማን ነው? ያለ ጌታስ በሕይወት ማን ይኖራል? ያለ ምግብ ሊንቀሳቀስ የሚችል ማን ነው? በክርስቶስ ኢየሱስ ሳይምንስ መንፈሳዊ እድገት የሚታይበት ማን ነው? ያለ ጌታ ወደ ጽዮን መድረስ መንግሥተ እግዚአብሔርን መውረስ የሚቻለው ማንም የለም።

በባዶ ሆድህ አትራመድ፣ ያለ ጌታ አትዙር፣ ኃይል አይኖርህምና። የሕይወት ረሃብተኛ አትሁን፣ ጌታ የሕይወት እንጀራ ነውና። አትራብ፣ የንጉሥ ልጅ ነህና።

አንባቢ ሆይ፥
ኤልያስን አስብ፤ እስራኤልንም ተገንዘብ፣ ለአንተ ከእስራኤልም ከኤልያስ ሕብስት የበለጠ ሕብስት፤ ከኤልያስ ጽዋ የበለጠ የሕይወት ጽዋ ተዘጋጅቶልሃል። ኢልያስ በምሳሌም ወደ እግዚአብሔር ተራራም ከደረሰ አንተማ ከአማናዊት ድንግል (መሶበ ወርቅ) የተገኘውን የሕይወት እንጀራ ተመግበህ (አምነህ) ለምን ወደ በኩራት ማኅበር፣ ወደ በጉ ዙፋን፣ ወደ አሸናፊዎች ከተማ አትደርስም? (ዕብ ፲፪፤፳፩)።

በባዶ ሆድህ አትራመድ፣ ያለ ጌታ አትዙር፣ ኃይል አይኖርህምና። የሕይወት ረሃብተኛ አትሁን፣ ጌታ የሕይወት እንጀራ ነውና። አትራብ፣ የንጉሥ ልጅ ነህና። (ሉቃ ፲፭፤፲፩-፴፱)። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በርታ።

፪ኛ) በእንጀራ (በምግብ) የሚመሰለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ጌታችን ለሰይጣን ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ቃለ እግዚአብሔርም ምግብ መሆኑን ተናገረ (ማቴ ፬፤፬ ። ሉቃ ፬፤፬)። ቅዱስ ኤርሚያስም «ቃልህን በላሁት» አለ (ኤር ፲፭፤፲፮)። የእግዚአብሔር ሰው ሕዝቅኤልም «የምሰጥህን ብላ አለኝ ... አጐረሰኝ ቃሉን በላሁት» ይላል (ሕዝ ፪፤፰-፲ ። ፫፤፩-፫)። ዮሐንስም በራእዩ የነቢያት ቃል ያጸድቃል «ራዕ ፲፤፰-፲)። ክቡር ዳዊትም «ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፣ ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» ይላል (መዝ ፻፲፰፤፩፻፫)። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጴጥሮስም በምግብ መስለው ቃሉን አስተምረዋል (ዕብ ፭፤፲፩፤፲፬ ።፩ኛ ጴጥ ፪፤፪-፫ ። ፩ኛ ቆሮ ፫፤፩-፬)።

መንፈሳዊ ሕይወትህን በረሃብ አትቅጣት። ነፍስህ ረሃብዋ የእግዚአብሔርን ቃል ማጣኒ ነውና። «ሲሲታ ለነፍስ ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ማለት የነፍስ ምግብዋ የእግዚአብሔር ቃል ነው» ተብሎ ስለተጻፈ ወንጌል ሳትሰማ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሳታነብ አትዋል። እግዚአብሔር በቅዱሳን ሰዎችና በመጽሐፍ ይናገራልና ስማው። ያን ጊዜ ያንተንም ጸሎት ይሰማሃል፤ እንባህንም ከፊትህ ያብስልሃል። እግዚአብሔር የሚሰሙትን ይሰማልና።

እግዚአብሔር ከሥጋና ከነፍስ ረሃብ ይጠብቀን። ... አሜን።